Fairfax County PUBLIC SCHOOLS
ENGAGE • INSPIRE • THRIVE

# የተማሪ ኮምፒውተር/መሣሪያ መውሰጃ መርሃግብር
# የቤት ውስጥ አጠቃቀም እና ሃላፊነትን የመቀበል ስምምነት

እኔ________________________________________ የ________________________________________

የወላጅ ወይም የአሳዳጊ ስም                                   የተማሪ ስም

በት/ቤታችን የኮምፒተር/መሳሪያ መውሰጃ መርሃግብር ተሳትፎ እፈቅዳለሁ ፡፡ ከዚህ በላይ ስሙ/ሟ የተጠቀሰው ተማሪ በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ ኮምፒተር/መሳሪያ ለመጠቀም እንደሚዋስምትዋስ አውቃለሁ፡፡

**ወላጅ/አሳዳጊ እና ተማሪው በሚቀጥሉት ሁኔታዎች ተስማምተዋል፡**

1. በተማሪ መብቶች እና ሀላፊነቶች በተዘረዘረው ተቀባይነት ባለው የአጠቃቀም ፖሊሲ መሠረት መሣሪያው በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ በሀላፊነት ጥቅም ላይ ይውላል።

2. መሣሪያው ከታች በፈረመው ተማሪ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

3. መሣሪያው ለመማሪያ ዓላማ ይውላል እንጂ ለመዝናኛ ወይም ለሥራ ስምሪት ተግባራት አይውልም፡፡

4. FCPS ከላይ ስሙ የተጠቀሰውን በመሣሪያ እንደገና መልሶ ጥቅም ላይ የዋሉትን ርእሶች እና የተቀመጡ የግል መረጃዎችን ጨምሮ በማኛውም ጊዜ የመፈተሽ መብት አለው።

5. ከ FCPS የትምህርት መርሃግብር ጋር የማይዛመዱ (የግል ጨዋታዎችን ወይም ሙዚቃን ማውረድ እና አፖችን ጨምሮ) መጠቀም የተከለከለ ነው።

6. መሣሪያው ከተመለሰ በኋላ ተማሪው በመሣሪያው ላይ ያከማቸው መረጃ ተመላሽ አይሆንም።.

7. ከዚህ በላይ የተጠቀሰው መሣሪያ ለተማሪዎች ጎጂ እና ተገቢ ያልሆኑ የበይነመረብ ጣቢያዎች እንዳያገኙ ለመገደብ የበይነመረብ ይዘት ማጣሪያ መተግበሪያ አለው። ወላጆች እና አሳዳጊዎች አሁንም የተማሪዎቻቸውን የ FCPS መሣሪያ አጠቃቀማቸው የመቆጣጠር ሃላፊነት አለባቸው።

8. መሣሪያው በጊዜያዊነት ለተማሪው ተውሷል፡፡ አስተማሪው ወይም ሌላ የትምህርት ቤቱ ባለሥልጣን ከጠየቁ መሣሪያው እና መለዋወጫዎቹ ወዲያውኑ ወደ ትምህርት ቤት ይመለሳሉ፡፡

9. ወላጅ / አሳዳጊ እና /ወይም ተማሪ ከዚህ በላይ ለተጠቀሰው መሣሪያ ሙሉ ሃላፊነት ይወስዳሉ፡፡ የተማሪው ግድየለሽነት ወይም የስነምግባር ጉድለት በተከሰተበት ሁኔታ ለተፈጠረው ማንኛውም ጥፋት ወላጅ / አሳዳጊ/ ዋጋውን ተመላሽ ለማድረግ ተስማምተዋል።

10. መሣሪያው ከጠፋ ፣ ከተሰረቀ ወይም ከተበላሸ ወላጅ / አሳዳጊ የሚተካው ወጪ ለFCPS ይመልሳል። ከፍያው መሣሪያው የተገዛበትን ዋና ወጪ አይበልጥም ፡፡ የጠፋ ፣ የተሰረቀ ወይም የተበላሸ መሣሪያ በሚኖርበት ጊዜ ወላጅ / ተማሪ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ መሳሪያውን ለመተካት የሚያስችል ተገቢ አሠራሮችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ት/ ቤቱን ማነጋገር ይኖርበታል፡፡

## ኃላፊነት ያለው የአጠቃቀም መመሪያዎች

## ከዚህ በታች ያሉት መመሪያዎች ከልጅዎ ጋር መታየት አለባችሁ፡፡

1. FCPS ያዋሰው የተማሪ መገልገያ መሳሪያ (ላፕቶፕ) ከFCPS የትምህርት ፕሮጀችት ጋር በተገናኘ ብቻ ጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡ እንደግል ወይም የማህበራዊ መገለገያ መሳሪያ ጥቅም ላይ መዋል የለበትም።

2. መገልገያ መሳሪያው በሚገባ መያዝ ይኖርበታል። መወርወር ፣ መመታት ወይም መጣል የለበትም። በፍፁም በመኪና ጣራ ወይም ኩዳን ላይ መቀመጥ፣ በእግረኛ መሄጃ በአስፋልት ወይም በማንኛውም መንገድ እንዲሰበር፣ እንዲወድቅ ወይም እንዲበላሽ መደረግ የለበትም።

3. የመገልገያ መሳሪያውን ለራሳቸው ብቻ ማዋል አለባቸው። ጓደኞች፣ ሌሎች ተማሪዎች ፣ወንድም/እህት፣ የአክስት/አጎት ልጆች ወይም ሌሎች ልጆች መጠቀም የለባቸውም። ሁልጊዜ ከቤት እንስሳዎች አርቃችሁ አስቀምጡ።

4. ተማሪዎች የመገልገያ መሳሪያውን በትምህርት ቤት፣ በዓውቶቡስ፣ በመተላለፊያ ቦታ/አዳራሽ፣ በምሳ መመገቢያ ቦታ፣ በእስፖርት መስሪያ ቦታ ወይም በማንኛውም ሕዝብ በሚሰበሰብበት ቦታዎች ያለ ጠባቂ መተው የለባቸውም።

5. የመገልገያ መሳሪያውን ውሃ አጠገብ፣ የቤት ውስጥ ኬሚካሎች፣ ምግብ እና መጠጥ ወይም ኤሌክትሮኒክስ የሆኑትን አካሎቹን ሊያበላሹ የሚችሉ ሌሎች ፈሳሽ ነገሮች አካባቢ ጥቅም ላይ መዋል የለበትም።

6. ውጭ በሚወሰድበት ጊዜ ኮምፒተር / መሳሪያ በዝናብ ፣ በበረዶ ፣ በከፍተኛ ሙቀት ወይም ቅዝቃዜ እንደማይጎዳ በሚያደርግ መንገድ መከላከል አለበት።

7. ኮምፒተር/መሳሪያ ሲጠቀሙ ኃላፊነት የሚሰማው የበየነመረብ ዜግነት ልምምድ ማድረግ አስፈላጊ ነው ። ኃላፊነት ያለው የበይነመረብ ዜግነ ተቀባይነት ያለው አጠቃቀም ፖሊሲ/መመሪያ ሰነድ በኢንተርኔት ደህንነት እና ጥበቃ ክፍል ውስጥ ተጠቅሷል።

8. የመገልገያ መሳሪያው ወደትምህርት ቤት ሲመጣ በየቀኑ ጥቅም ላይ እንዲውል ባትሪው ሙሉ መሆን አለበት።

9. ለተመረመሩ/ለተወሰዱ ኮምፒውተሮችቴክኒካዊ ድጋፍ በትምህርት ሰአት ብቻ ይሰጣል።

ከላይ የተጠቀሱትን ቅድመ ሁኔታዎችንና መመሪያዎችን አንብቤ ተስማምቻለሁ። ልጄ የFCPS ላፕቶፕ እንዲሰጠው/ጣት ፈቅጃለሁ።

የወላጅ / አሳዳጊ ስም (እባክዎን ይጻፉ) ______________________________

የወላጅ / አሳዳጊ ፊርማ (እባክዎን ይፈርሙ) ______________________________

የዛሬ ቀን ____________